# የነ ዶ/ር አብይ ለውጥ "ታጥቦ ጭቃ እንዳይሆን"

ባለፉት ጥቂት ወራት የዶ/ር አብይን የለውጥ መንፈስ አይተን ልባችን የተሰፋ ምቱን ባያቋርጥም ሰሞኑን የምናያቸው እና የምንሰማቸው ዜናዎች የውስጥ ሰላም የሚሰጡ አይደለም። ዶ/ር አብይን እንደግፋለን እያሉ ከውጭም ከውስጥም የሚሰባሰቡትን ሃይሎች በዜና ማሰራጫዎች ስናይ ትላንት ኢትዮጵያዊያንን በቋንቋ ከልለው እንዲጠላለፉ ትልቅ መሰረት የጣሉት የወያኔ/ኢህአዴ

አጃቢዎች፤ የኢህአዴግን ህገ መንግስት አርቅቀው ያጸደቁት ባለውለተኞች፤ ጀኔራች ተብለው በህዝባችን ላይ ሲያዘምቱ የነበሩት የጦር አለቆች፤ባለፉት አመታት ያን ያህል ትግል ሲደረግ ዳር ቆመው ያደፈጡት አድርባዮች እና ወያኔን አምላኪዎች የነበሩ ሰዎች መሆናቸው እያሳሰበን ነው። እነዚህም ሃይሎች ከየአቅጣጫው መድረኮቹ በብቸኝነት ተሰጥቷቸዋል በዚህም እድላቸው ተጠቅመው የትግሉን አቅጣጫ ሊያሳዩን ሲሞክሩ በማየታችን

ባችን ቆስልዋል። አዎን ለብዙ ዓመታት በርካታ ኢትዮጵያዊያን የደከሙለትን እና መስዋእትነት የከፈሉለትን የሰላም እና እርቅ አጀንዳ የዴሞክራሲ እና እኩልነት ጥያቄ በኢህአዴግ መሪ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ በዶ/ሩ ግንባር ቀደም አቀንቃኝነት የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም ወጣቱ በዚህ መንፈስ እየነጎደ መታየቱ የሚያስደስት ቢሆንም በየመድረኩ ብቅብቅ የሚሉትን የድል ቀን አርበኞች ስናይ የትግሉ ውጤት "ታጥቦ ጭቃ" እንዳይሆን የውስጥ ሲቃ ይፈጥርብናል።

ባለፉት ወራት የዶ/ር አብይን "የእንደመር" ጥሪ ተቀብለናል ብለው ከውጭ ወደ አዲስ አበባ እየበረሩ የሚገቡትን ሰዎች ፍጥነት ሰናይ ከውስጥም ከተደበቁበት ጐሬ ብቅ ብቅ የሚሉትን የድል ቀን አርበኞች ስናስተውል ዝም ብለን እንድንቀመጥ የሚጋብዝ ይደለም። ለማስታወስ ያህል የኢትዮጵያን ህዝብ በቋንቋ ያካለሉት ዋናዎቹ ሃይሎች እነ አቶ ሌንጮ፤ ህዝባችን በተለይ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተክርስትያን በማዳከም የሚታወቁት አማራውንና ጉራጌውን ከምስራቅ ኢትዮጵያ ያስጨፈጨፉት እና ያፈናቀሉት እነ አቶ ታምራት ላይኔ እና ሌሎችም የአቶ መለስ ወዳጆች ከዚህም አልፎ የመንግስቱ ኃ/ማርያም ቀኝ እጅ የነበሩ ሰዎች ከኢህአዴግ ጋር ውስጥ ለውስጥ እየተደራደሩ በሩጫው እንዳይቀደሙ ቀድመው ከኢህአዴግ በር በመቆም በዜና ማሰራጫዎቹ እና በየመድረኮቹ አለሁ አለሁ ብለው አሉ እየተባሉ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም ትላንት የኢህአዴግ መሪዎች እና የጦር ጀኔራሎች የነበሩት ጉዶች(እነ ጻድቃን) ቅድሚያ እድል እየተሰጣቸው የትግሉን አቅጣጫ እናመላክታችሁ እያሉን ነው፤ ዛሬም የነዶ/ር አብይ ሚድያ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች እምብዛም እድል ሲሰጥ አይታይም ሌሎች ሚድያዎችም ቢሆን ከተመሳሳይ ድክመት አልጸዱም ሁሉም የተለየ ሀሳብ ለመስማት ገና አልተዘጋጁም። እጅግ የሚያሳዝነው የለውጡ ዋነኛ ሃይሎች ከፍተኛውን መስዋእትነት የከፈሉት እና ህዝቡ መሆኑ እየተረሳ ኢህአዴግ እና በአንድ ወቅት ከአቶ መለስ ጋር የተኮራረፉ ሰዎች እየሆኑ ነው። በየከተሞቹ በተካሄዱት ሰልፎች መድረኩ ለታጋዮቹ መስዋዕትነት ለከፈሉት ሳይሆን ለኢህአዴግ ባለስልታኖች ብቻ መሆኑን ላስተዋለ ስጋት ላይ ይጥላል ።አሁንም ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያዊነት የቆሙት ሃይሎች ብዙም ትኩረት አልተሰጣቸውም።

ደግሞ የሚገርመው እነዚህ የቀድሞ የኢህአዴግ ወዳጆች የፖለቲካውን መድረክ ለመቆጣጠር ሲሞክሩ ከዚህ በፊት በሰሩት ስህተት ለተጎዳው ህዝብ ስህተታቸውን በግልጽ አምነው በመቀበል ይቅርታ ሲጠይቁ አይሰሙም፤ እነዚህ ሃይሎች ባለፉት ዓመታት ለህዝባችን መብት እና እኩልነት መከበር የተደረገውን ትግል እና ለተከፈለው መስዋእትነት እውቅና ሰጥተው ከህዝብ ጎን እንቆማለን ከማለት ፋንታ በግል እና በቡድን ስህተታቸው ምክንያት ወይም በግል ችግራቸው ምክንያት የድሮ ወዳጆቻቸው ያደረሱባቸውን በደል ከማውራት አልፈው የይቅርታ መንፈስ አይታይባቸውም።

እነዚህ ሰዎች በተመቻቸላቸው አጋጣሚ "ዶ/ር አብይን ለመርዳት ዝግጁ ነን" ሲሉ ሰንሰማ ተረት ተረት ይሆንብናል። ወይስ ኢህአዴግ በየጊዜው እንደሚለው "አዎ ብዙ ነገሮችን አበላሽቻለሁ ግን እኔ ብቻ ነኝ ማስተካከል የምችለው ሌሎቻችሁ አትድረሱብኝ" እያለ ከጭቃ ወደ ጭቃ የሚዳክረው ኢህአዴግ ባህል ልምድ ሰላላቸው በለመዱት መንገድ መሄዳቸው ነው? እንግዲህ እነ አቶ ታምራት በዚህ መልክ ካሰቡ ዘግይተዋል፤ ወይም ደግሞ ለዘመናት ለኢትዮጵያ ህዝብ መብት መከበር ሲታገሉ የቆዩትን ሃይሎች ከነዶ/ር አብይ ሳይገናኙ እንቅደማቸው የሚል ስሌትም ከሆነ የሚያዋጣ አይመስለኝም። ለዶ/ር አብይም ቢሆን በነዚህ ሰዎች መከበብ አይጠቅማቸውም።

መቼም የተለያዩ ዜናዎችን እንደምንሰማው በቡድን(ድርጅት)ም በተናጠልም የገቡትም ሆነ ለመግባት በዝግጅት ላይ ያሉት ሃይሎች ባለፉት ዓመታት ባደረግነው ትግል የግል ማንነታቸው እና የድርጅታቸው የበላይነት አባዜ ቀፍድዶ ይዟቸው ጠንካራ የተፎካካሪ ሃይል እንዳይፈጠር ከግራ ከቀኝ ወጥረው ደንቀራ ሆነው የቆዩትም ሃይሎች ጭምር በመሆናቸው ሳይገርመን አይቀርም። እነዚህ ሃይሎች ሲረግጠን ከነበረው ኢህአዴግ ጋር ለመታረቅ ይህን ያህል ቅን ልቦና ካላቸው ለምን የተቃዋሚው ሃይል መሰረታዊ በሆኑ መርሆች ላይ ስምምነት ፈጥሮ (የግድ

ባንድ ድርጅት ስር መሆን አይጠይቅም) በጋራ እንዲታገል ከማድረግ ፋንታ አንዱን ሲያቅፉ አንዱን ሲገፉ እንደቆዩ አይገባኝም። አሁንም ይህን የተናጠል እሩጫቸው ካላስቆምናቸው ተጠቅተው ያስጠቁናል።

አዎን ይሄን በታሪካችን በተደጋጋሚ አይተናል፤ ደርግ ከስልጣን ሲወጣ እንደግፈው ብለው የተቀላቀሉት ሃይሎች ህዝብንም እራሳቸውንም አስጨርሰዋል፤ ከወያኔ ጋር የገባው ኦነግ መጨረሻው በብዙ ሺ የሚቆጠር የኦሮሞ ልጆችን ህይወት ዋጋ አስከፍሎዋል ሌሎቹም ቡድኖች እና ግለሰቦች ሲዋረዱ እንጅ ለውጤት ሲበቁ አላየንም ይልቁንም በነሱ ድጋፍ የተደላደለው መንግስት ይህን ያህል ዘመን ይህን ሁሉ እልቂት እንዲፈጽምብን አድርገውታል።

በርግጥ ዶ/ር አብይን እንደ ደርግ ወይም ወያኔ መሪዎች አልጠረጥረውም፤ ቅን ልቦናውን ህሊናዬ ይቀበለዋል ስጋቴ እና ፍርሃቴ ግን "የገብያ ግርግር ለሌባ ያመቻል" እንዳይሆን ነው። ዶ/ር አብይ እና በዙሪያው የተሰለፉት ሃይሎች ለውጥ ለማምጣት ቁርጠው የተነሱ ቢመስሉም ለውጡን ከግቡ ለማድረስ ያላቸው ድርጅታዊ ብቃት እና የድርጅታዊ ስራቸው ስፋት እና ጥልቀት የሚያስተማምን አይደለም፤ እንዲያውም ያው የገለማው ኢህአዴግ ውጤቶች በመሆናቸው ያሳቅቃል። የዶ/ር አብይን የለውጥ መንፈስ በሰፊው እያሟሟቀ ያለው ያደራጁት ሃይል ሳይሆን በብሶት ላይ የነበረው ህዝብ ነው በተለይም ወጣቱ።

በድርጅታቸው ዙሪያ ከጥቂቶች በቀር ብዙሃኑ እንደተደናገጡ ናቸው። ይህን የለውጥ መንፈስ ለማስፈጸም በቆራጥነት እና በጥራት ተደራጅቶ የሚንቀሳቀስ ሃይል አለመኖሩ ትልቅ ክፍተት በመሆኑ ያልተዘጋ አጀንዳ ያላቸው ሃይሎች የዶ/ር አብይን ቅን መንፈስ በመጠቀም ሰርገው በመግባት አደጋ ላይ እንዳይጥሉን እሰጋለሁ(የጎርባቾብን እና የሶብየት ህብረትን ታሪክ እናስተውስ)። እነዚህ ሃይሎች በተለይ በውጭ የቆዩት ለውጡን በፍጹም ቅንነት የሚቀበሉት ከሆነ ለዚህ ለውጥ ሲታገሉ የቆዩትን ሃይሎች ሁሉ በማስተባነር ከህዝብ ጎን አሰልፈው ከኢህአዴግ ባሻገር ተጽእኖ ፈጣሪ የለውጥ ሃይል መፍጠር ሲገባቸው ጓሮ ለጓሮ ከኢህአዴግ ጋር የሚነጋገሩበት ምክንያት አይገባኝም።

አዎን በነዶ/ር አብይ አይፈረድም እየሮጠ የሚገባውን ሁሉ ማስተናገድ አለባቸው፤ አሁንም ውጭ ሆነው መንገዳቸውን እያስተካከሉ ያሉትንም በጓሮ በር ቢያነጋግሩ አይገርምም፤ ዶ/ር አብይ አሁን ከፍተኛ ችግር አለባቸው ኢህአዴግን ቀጥ አድርገው እየመሩት ነው ብሎ የሚጃጃል የለም፤ እንዲያውም ኢህአዴግ እንደ ድርጅት የአስተሳሰብ አንድነት የሌለው መሆኑን በግልጽ እያየን ነው፤ ድርጅታዊ ዲሲፕሊን ከሞተ ቆይትዋል። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ያለን ድርጅት ይዘው እነዶ/ር አብይ በተወሰኑ ሰዎች ድጋፍ ለውጤት ይበቃሉ ብሎ የሚጠባበቅ ካለ ስህተት ይሆናል።

ይሄንም የተረዱት ዶ/ር አብይ ደካማ ጎናቸውን ለመሸፈን የሚወስዱዋቸውን እርምጃዎች የሚደግፉትን ሃይሎች ሁሉ በደስታ እየተቀበሉ ነው። ለዚህም በአንድ ወቅት የኢህአዴግ ወዳጅ እና አጋር የነበሩት እና በኢህአዴግ ውስጥ በተለያዩ ስልጣናት ላይ የነበሩት አንዳንድ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በሰልፉ ቀዳሚውን ቦታ እየሰጥዋቸው ነው። ብዙዎቹ ከነ አቶመለስ ቡድን ጋር በጥቅም ወይም በስልጣን የተጋጩ ናቸው አንዳንዶቹ ደግሞ በሆዳምነታቸው፤ ታድያ በዚህ መልክ ወደ ዳር የቆዩትን ሃይሎች ዶ/ር አብይም ሆነ ሚዲያዎቻቸው ሲያሸሞነሙኑዋቸው ሰናይ አደጋው የበለጠ ጎልቶ ይታያል። ለዚህም ምሳሌ በአቶ ኢሳያስ አፈወርቅ አቀባበል ላይ አቶ ታምራት ላይኔ እንደ ክብር እንግዳ ተቆጥረው በዶ/ር አብይ አንደበት "የተከበሩ አቶ ታምራት ላይይይኔ" ሲሉ የዶ/ር አብይ የድምጽ ቅላጼ የሚገርም ነበር፤ ይህን ሲያደርጉ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚደሰት መስሎዋቸው ከሆነ ደግሞ ተሳስትዋል፤ በጣም ተሳስተዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ አቶ ታምራትን ከነወኔው በደንብ አርጎ ያውቀዋል።

ይሽ ይሁንና አቶ ታምራትን "ክቡር" ካልን ለህዝብ መብት መስዋእትነት የከፈሉትን እነ ፕሮፈሰር አስራትን እነ እስክንድር ነጋን እነ አንዱዓለምን እነ በቀለ ገርባን እነ ንግስትን እነ ጫልቱን ምን እንበላቸው፤ አሁንም ለመከበር እና የክብር ቦታ ለማግኘት የግድ በኢህአዴግ ማለፍ አለብን? አዎን ሰለ ሰላምና እርቅ የሚሰጡትን ትምህርት እወደዋለሁ በዚህ መልክ ሲሆን ግን "እርቅንም ይቅርታንም" ያራክሰዋል። እንዲያው ከተነሳህበት ጉዳይ ወጣህ ካላላችሁኝ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ዶ/ር አብይ ያለአግባብ ሲቻኮሉ እና አንዳንድ አነጋጋሪ ስራዎችን ሲያካሂዱ ይታያል ለምሳሌ ከኤርትራ ህዝብ ጋር የተደረገው ህዝባዊ ግንኙነቶች እና እርቅ እጅግ የሚያስመሰግናቸው እና የሚያስደስት ቢሆንም አቶ ኢሳያስን በተመለከተ ይሰጥ የነበረው አስተያየትና ፕሮፖጋንዳ ከሚገባው በላይ ይለጠጥ ነበር ድርድሩም እንዲያው እንደነ አቶ መለስ ዘመን ክፍት ሆኖ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ እንዳይሰጥ እሰጋለሁ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ መንግስታት ጋር ጥሩ ግንኙነት ለማድረግ በሄዱት ፍጥነት ይህ ለውጥ እንዲመጣ የታገሉትን እና መስዋእትነት የከፈሉትን ሃይሎችን በማቅረብ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮ መወያየቱ ገና አልተሞከረም እንዲያውም እራሱ ኢህአዴግ የኢህአዴግ ተቃዋሚ እንደሆነ ተደርጎ ከጥላው ጋር እየነጎደ ነው። እስከ መቼ ዶ/ር አብይ???

እንግዲህ ይችን ጽሁፌን ሳጠቃልል ሁለት ሃሳቦችን አጉልቼ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ

አንደኛ: ምንም እንኳን እነ ዶ/ር አብይ የኢህአዴግ አባላት ቢሆኑም ዛሬ እነ ዶ/ር አብይን በዚህ ስነልቦና የወለደቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ነው፤ ህዝባችን የተፈጸመበት ግፍ የከፈለው መስዋዕትነት ህሊና ላለው ሰው በጣም ከባድ ነው። ታዲያ ይህን ከብዙ መስዋዕትነት ቦኋላ በጣም ወሳኝ በሆነ ወቅት የተገኘ ዕድል የድሮ ኢህአዴግ ልጆች እና ወዳጆች አጅበውት ለውጤት ይበቃል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ ትልቅ ስህተት ይሆናል፤ ሰለዚህ እነ ዶ/ር አብይ የትኩረት አቅጣጫ ቸውን በፍጥነት በማስተካከል ሰፊውን የኢትዮጵያ ህዝብ እና በትግል ላይ የቆዩትን ተፎካካሪ ሃሳብ እና የመፍትሄ መንገድ አለን የሚሉትን ሁሉንም ወገኖች በሙሉ የሚያሰባስብ መድረክ በመፍጠር ፊትለፊት እየተገናኙ ገንቢ ስራ እንዲሰሩ እንደ አንድ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ እማጸናቸዎለሁ፤ ይህም ተግባራዊ እስኪሆን ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የዜና ማሰራጫዎቹ ከኢህዴግ ውጭ ለሆኑት ሃይሎች ይበልጥ ክፍት ሆነው ሰፊ ውይይቶች እየተደረገባቸው ቢቆዩ ለሁላችንም የሚጠቅም እና የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። ካለዚያ ይህ ሞቅሞቅ ከአንድ ቦታ ላይ አደጋ ሊያጋጥመው ይችላል፤ መቸም በሀገራችንም ሆነ በዓለማችን ስንት ህዝባዊይ እና ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች በአስመሳዮች እንደከሸፉ የሚዘነጋ አይሆንም።

ሁለተኛ: በጥቅሉ ባለፉት ዓመታት በተለይ ደግሞ የለውጡ ቋያ በተቀጣጠለበት ባለፉት ወራት ተፎካካሪ የሚባለው በትግል ላይ የቆየው ሃይል ሚና በጣም ደብዝዞ ይታያል። እንዲያውም አሁንማ ኢህአዴግ ዛሬ ምን አለ፤ ነገስ ምን ያደረግ ይሆን እያልን ኢህአዴግ ገዳይ ኢህአዴግ የለውጥ አርበኛ ሆኖ ከጥላው ጋር የሚሮጠውን ኢህአዴግ፤ አቅጣጫው የጠፋበትን ኢህአዴግ አጅበን የምንከተል እንመስላለን። ተፎካካሪዎቹ ድርጅቶች ትግሉን ሲመሩት አይታይም ህዝቡ ነው ድርጅቶቹን እየመራቸው ያለ፤ ይህ በአስቸኳይ መለወጥ አለበት። ለውጡ በአስመሳይ አውሬዎች ተጠልፎ ከከፍተኛ አደጋ ላይ እንዳንወድቅ በትግል ላይ የቆዩት ሀይሎች የድርጅት አጥራቸውን አፍርሰው የመሪዎቹን የገነነ ተክለሰባዊ ናፍቆት አስወግደው በመሰባሰብ አማራጭነቱንም ሆነ ለውጥ ፈላጊነቱን ማሳየት አለባቸው።

አሁንም ኢህአዴግ እየደከመ እና እየፈረሰ ሥለሆነ የኔ ድርጅት ትልቅ ቦታ ለማግኘት እድል አለው በሚል ስሌት ድርጅታቸውንና አባላቶቻቸውን ከሌላው በመለየት ለመንጎድ የሚፈልጉ የድርጅት መሪዎችን አሁንስ አበዛችሁት ካላልናቸው መረማመጃ ያደርጉናል። በድርጅት የታቀፋችሁ ወገኖች ትንሽ ትልቅ ሳትሉ ከሌሎች ድርጅቶች እና አባላት ጋር በመተባበር እና በመከባበር የጋራ መርህ ይዞ ለመውጣት መሪዎቻችሁን ማስገደድ አለባችሁ።

ብዙውን ጊዜ መሪዎች በሌለ ወንበር እየተስገበገቡ ስልጣን ላለመጋራት ድርጅታቸውን እና አባሎቻቸውን ከሌሎቾ ድርጅቶች አባላት ጋር እንዳይገናኙ በሌሎቹ ላይ ያልሆነ ስም ለጥፈው ሲያራርቁ አይተናል። ይህ ፍጹም መወገድ ያለበት ባህል ነው፤ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮዮጵያ ትልቅ ነኝ ለሚለውም ሆነ ለትንሹ ድርጅት፤ ለተደራጁም ሆነ ለግለሰቦች የምትሰጠው ሰፊ እድል አለ። ሰለዚህ እያንዳንዱ የሚኖረውን ድርሻና ሚና አቀናጅቶ ለውጤት ከመስራት ፋንታ በጓሮ በር ከኢህአዴጎች ጋር በመላላክ ትግሉን የጥሎ ማለፍ እሩጫ ለማረግ የሚሞክሩትን ሃይሎች ልናስቆማቸው ይገባል። ይህን ማድረግ የምንችለው በትግሉ የቆዩትን ሙህራን፤ አገር ወዳዶች እና ሁሉንም ድርጅቶች በአንድ መድረክ በማገናኘት ሁሉንም የሚያስማማ አንድ የጋራ ሰነድ አዘጋጅተው ለዚያ ተገዢ ስንሆን ብቻ ነው።

ይህን ስናደርግ ለውጥ እንፈልጋለን የሚሉት የኢህአዴግ ሃይሎች በክብር በቦታችን ይቀበሉናል እኛም ከኢህአዴግ የተሻለ ለውጥ አምጭ መሆናችን እናሳያለን፤ ያኔ ሃገራችን እየነጎደችበት ባለው የፖለቲካ ለውጥ ጥሩ ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን ይቻላል። እንደዚህ ስናደርግ የትግሉ አቅጣጫ ትክክለኛውን እና አስተማማኝ መስመር ይይዛል፤ እንደዚህ ስናደርግ ለትግሉ የተከፈለው መስዋዕትነት ትክክለኛውን ዋጋ ያገኛል።ካለዚያ ከየ ጠርዙ ቁጭ ብለን እነዶ/ር አብይ ይሄን ያድርጉ እነ ዶ/ር አብይ በዚህ ገቡ እነ ዶ/ር በዚህ ወጡ ትላንት እዛ ነበሩ ዛሬ እዚህ መጡ እያልን ከኢህአዴግ መና የምንጠብቅ ከሆነ የተኙት የቀን ጅቦች ለመልከስከስ የሚሯሯጡትን ውሻዎች ተጠቅመው የለውጡን አቅጣጫ ያስቱታል። ሰለዚህ ይህ ትግል ታጥቦ ጭቃ እንዳይሆን ከኢህአዴግ በላይ የሚያስተማምን ከኢህአዴግ በላይ ትልቅ ህልም ያለው ሃይል እንዲፈጠር ህዝቡ ታጋዩችን በመግራት ተጽዕኖ ማሳደር አለበት፤ አንዳንዴ የሚታየው ሆያሆየ ቆም ብሎ የቡድን ስሜት ተሸንፎ ሁሉንም የሚያሳትፍ መድረክ ተፈጥሮ ትግሉ ለውጤት እንዲበቃ እንደነ ኢሳት ያላችሁ የመረጃ ምንጮች ብዙ ብንጠብቅባችሁም ገና ግዳጃችሁን አልተወጣችሁም።

ተስፋሁን አረጋይ